# የለውጥ /የአለመረጋጋት/ ወቅት እና የጥፋት ስጋት

(ከአርአያ ንጉሴ)

ባለፉት ሁለቱ ሰላማዊ ባልሆኑ የስርአት ለውጦች ኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉባቸው ወቅቶች በሰው እና በንብረት ላይ ጥፋት ደርሷል። ባለፉት ሶስት አመታት አካባቢ በሆነው እና በተለያዩ ክልሎች በተካሄደው ህዝባዊ አመጽ ወቅት እንዲሁ በሰው እና በንብረት ላይ ጥፋት ደርሷል። ካሁኑ ጥንቃቄ ካልተደረገ የደረሰው ጥፋት መደጋገሙ አይቀርም የሚል ስጋት አለ።

ስልጣን ከንጉሡ ወደ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት በአመጽ/በአብዮት/ በተዛወረበት ወቅት እና የሥርአት ለውጥ ሲደረግ፤ የመሬት ባላባት፥ ፊውዳል፥ አድሀሪ ወ.ዘ.ተ. . .እየተባሉ ሰዎች ተገድለዋል። ንጉሡን እና የወቅቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ጨምሮ በርካታ ግለሰቦች በራሳቸው ሃገር ዜጋ ተገድለዋል። መሬቴን እና ጠብመንጃዬን አላስረክብም በማለት ዱር ገብተው ተዋግተው የሞቱም አሉ። በተጨማሪም "የመሬት ላራሹን እና የትርፍ ቤቶችን አዋጅን" ተከትሎ መሬታቸውን እና ንበረታቸውን ያለምን ካሳ ሳያገኙ። ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩበት ተመጣጣኝ የንብረታቸውን ድርሻ ሳያገኙ በርካታ ሰዎች ከንብረታቸው ተሰናብተዋል። እስከ ዛሬ ድረስ አንዱም የኢትዮጵያ መንግስት ሳያስታውሳቸው ከቤት እና ንብረታቸው ወጥተው ቀርተዋል። በዚሁ ደም ባፋሰሰ የሥርአት ለውጥ ወቅት፤ ሰዎች በነበራቸው የመደብ፣ የፖለቲካ አመለካከት፥ በነበሩበት የፓሊቲካ ድርጅት፥ በቂም በቀል፥ ወ.ዘ.ተ...ምክንያቶች ተገድዋል። ተገድለው መንገድ ላያ ተጥለዋል። ሌሎች ድርጊቶችም ተፈጽመዋል።

ስልጣን ከደርግ-ኢሠፓ ወደ ኢህአዴግ መራሹ ሽግግር መንግስት በጦርነት እና በደርግ-ኢሠፓ የተሳሳተ አመራር በተዛወረበት ወቅት እና የሥርአት ለውጥ ሲደረግ፤ እንዲሁ ሰዎች በብሔራቸው፥ በፓለቲካ አመለካከታቸው፥ በቂም በቀል እና በሌሎች ምክንያት ተገድለዋል። ገደል ውስጥ ተወርውረዋል። በስለት እቃ ተወገተው ሞተዋል።

በዚሁ ወቅት የግለሰቦች ንብረት ተዘርፏል። በአንዳንድ ከተሞች የመንግስት መስሪያ ቤቶች የቢሮ እቃዎች ተዘርፈዋል። የገበሬዎች ህብረት ስራ ማሕበራት የጋራ ሱቆች ተዘርፈዋል። የገበሬዎች ህብረት ስራ ማሕበራት የጋራ ወፍጮ ቤቶች በአካባቢ ገልሰቦች ተነቅለው ተወስደዋል። በኋልም የአካባቢው ነዋሪዎች በእግር ጉዞ ሩቅ ቦታ ለማስፈጨት ተገደዋል።

የጥፋት ዘመን-ከ1983 እስከ 2007 ዓ.ም. በዐማራ ሕዝብ ላይ የተፈጸመ ዘር ማጽዳት-በሚል አርዕስት። በ2008 ዓ.ም. የታተመ፥ መታሰቢያነቱ ለፕሮፌሰር ዐሥራት ወልደየሥ ያደረገ እና በሙሉቀን ተስፋ የተጻፈ መጽሐፍ በወቅቱ የነበረውን ጥፋት ያስረዳል። የደረሱትን በርካታ የጥፋት ድርጊቶች የመዘገበ እና አድካሚ በሆን መንገድ የተዘጋጀ መጽሐፍ መሆኑ ያስታውቃል። ሆኖምን የደረሱት ሁሉንም መዝግቧል ማለት አይቻልም። እኔ እንኳን የማውቃቸው። መጽሐፉ የጠቀሳቸው ቦታዎች ውስጥ ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎች ነገር ግን ያልተጠቀሱ አሉ።

**የለውጥ/የአለመረጋጋት/ ወቅት እና የጥፋት ስጋት-በኦሮሚያ።**

በቀድሞው አጠራር ከሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት/ክፍለ ሐገር/ እስከ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት /ክፍለ ሃገር/ ያለውን የኢትዮጵያን ክፍል እና ኢህአዴግ የኦሮሚያ ክልል /ክልል 4/ ብሎ በሰየመው ክልል። በአቀማመጡ እና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ -ካሉት 9 ክልሎች መሃል - ይህ ክልል በርካታ ብሔረሰቦች አሉበት። ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ ባለፉት አመታት በወሰዳቸው አሉታዊ እርምጃዎች የተነሳ በተፈጠረ ብሶት እና ጤናማ ያልሆነ አመለካካት ላይ ሰላማዊ ባልሆነ መልኩ የስርአት ለውጥ ቢካሄድ ወይም በሌላ ምክንያት አለመረጋጋት ቢፈጠር። በዚህ ወቅት በክልሉ ሰው እና በንብረት ላይ ጥፋት ሊደርስ ይችላል የሚል ስጋት አለ።

የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች ተወላጆች አጎራባች በሆኑት እና ኦሮሚያ ክልል ባሉ ከተሞች ውስጥ በስራ ምክንያት ሲኖሩ። የጉራጌ ብሔር ተወላጆች እና የትግራይ ብሔር ተወላጆች በተለያዩ ኦሮሚያ ክልል ባሉ ከተሞች ውስጥ ይኖራሉ። እንዲሁም በክልሉ በብዛት ሁለተኛ ደረጃ የሚይዙት የአማራው ብሔር ተወላጆች ኦሮሚያ ክልል ባሉ ከተሞች ውስጥ እና በኦሮሚያ ገጠሮች ውስጥ ተበታትነው

ይኖራሉ። በተጨማሪ የአርጎባዎ ብሔር ተወላጆች፥ የሶማሌ ብሔር ተወላጆች እና የሌሎች-ብሔር ተወላጆች እዚህ ክልል ውስጥ ይኖራሉ።

ኢህአዴግ ሃገሪቱን በተቆጣጠረ 1983 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ አመታት፤ ኦነግ፥ ኢህአዴግ እና ሌሎችም የኦሮምን ሕዝብ እንወክላለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን ክልል የሃላፊነት ድርሻቸው ግልጽ ባልሆነ መልኩ ያስተዳድሩ ነበር። ኦነግ ከሽግግሩ መንግስት ከወጣ በኋላ እና የኢህአዴግ ሰራዊት /በአብዛኛው የህወሃት ሰራዊት/ ክልሉን ተቆጥጥሮ ለኦህዴድ/ኢህአዴግ/ አስረክቦታል።

ከዚያ ጊዜ ወዲህ የዚህን የክልል ፓለቲካ ፥ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል/አልፎ አልፎ የህወሀት ካድሬዎች እና የጸጥታ ክፍሎች ገባ ወጣ ከማለት በስተቀር/ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ይቆጣጠር ነበር። በእነኚህ 27 አመታትም በዚህ ክልል አንጻራዊ ሰላም ነበር ማለት ይቻላል። ካለፉት ሶስት አመታት በተረፈ። እነኚም ቢሆኑ ካለ ኦህዴድ እውቀት እንዳልተደረጉ ብዙ ግምቶች አሉ።

ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ በእነኚህ አመታት በክልሉ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ እና እኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ያደረሰው አሉታዊ እና አዎንታዊ ለውጦች በዚህ ጽሁፍ ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደለም።

በተለይ እዚህ ክልል ውስጥ በሚገኙ የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ቋንቋ፥ ባህል፥ በቀበሌ እና በከተማ አስተዳደር  የመምረጥ እና የመመረጥ-መብት። በህዝባዊ እና በመንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ በችሎታ ለከፍተኛ ሃላፊነት የመብቃት መብት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ የወሰዳቸው አሉታዊ እርምጃዎች። በክልሉ በሚገኙ የሌሎች-ብሔሮች ተወላጆች ውስጥ ብሶት፥ ቅሬታ እና መበደል ስሜት ፈጥሯል።

የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ቁጥር አብላጫ  በሆኑበት ከተማዎች እንኳን ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ ሌላ አማራጭ የስራ ቋንቋ አልሰጠም።  አልፎ አልፎ በሕዝባዊ ድርጅቶች እና በግል ድርጅቶች ሌሎች ቋንቋዎች ተደርበው ከማገልገል  ሌላ፤ ኦሮምኛ ብቻ በላቲን ፊደላት እየተጻፈ የክልሉ የስራ ቋንቋ ሆኖ በየመስሪያ ቤቱ ያገለግላል።

ችግሩ ኦሮምኛ ቋንቋ የስራ ቋንቋ መሆን አይደለም ወይም የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ኦሮምኛ ቋንቋ ማወቅና እና መጠቀም አይደለም ወይም  የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ኦሮምኛ እንዲማሩ መደረግ አይደለም። በክልሉ የሚገኙ ሌሎች-ብሔሮች አማራጭ የስራ ቋንቋ የመጠቀም መብት አለመሰጠት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች/በተለይ በገጠር ለሚኖሩ ወጣቶች/ ለስራ ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ሌላ ክልል ሲሄዱ መግባባት እንዲችሉ ተጨማሪ ቋንቋ ስልጠና አለመሰጠት ነው።

በተለይ በገጠሩ ኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ሌሎች-ብሔሮች አዲስ ትውልድ በዚህ በ27 አመታት የራሳችን ቋንቋ የሚሉተን አስተካክለው አይናገሩም።  ማታ ቤት ሲገቡ  ከዋላጆቻቸው ከሚሰሙት ሌላ አብዛኞቹ የራሳችን ነው የሚሉትን ቋንቋ አይማሩም። እነዚህ ወላጆች ሲያልፉ ከነሱ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ቋንቋው፣ ባሕሉ እና ሌሎችም ነገሮች ጠፉ ማለት ነው።

በተጨማሪ በቀበሌ እና በከተማ አስተዳደር ። በህዝባዊ እና በመንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች ሃላፊዎችን  የሚመድበው ኦህዴድ/ኢህአዴግ/ ሲሆን፤  ግለሰቦቹም የኦህዴድ/ኢህአዴግ/ ወይም በእነሱ አባባል የድርጅት አባሎች መሆን አለባቸው። በዚህም የተነሳ የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ላይ መብቶች ተነፍገውኛል የሚል ብሶት ፈጥሯል።

ካሉት ሃገር አቀፍ ችግሮች በተጨማሪ፤ ኦህዴድ ኢህአዴግ/ ባለፉት አመታት በተከተለው አሉታዊ እርምጃዎች የሌሎች-ብሔር ተወላጆች ላይ ብሶት ሲፈጥር። ማለት በተወለድኩበት፥ ባደግኩበት እና በሃገሬ፤ ቋንቋዬ ስራ ላይ ማዋል አልቻልኩም፥ ባሕሌ ተበድሏል እና መብቶች ተነፍገውኛል የሚል ብሶት ሲፈጥር። በሌላ በኩል ኦህዴዲ/ኢህአዴግ/ለ27አመታት ባደረገው ሰፊ ቅስቀሳ/በተለይ በምርጫ 97/፥ ባሰራቸው ሃውልቶች እና ሌሎች መንገዶች፤ አብዛኛው የኦሮሞ ተወላጆች ውስጥ በተለያዩ

መልክ እየተገለጹ ያሉ ጤናማ ያልሆኑ አመለካከቶች ፈጥሯል። እነዚህ ብሶቶች እና አመለካከቶች ላይ ሰላማዊ ባልሆነ መልኩ የስርአት ለውጥ ቢካሄድ ወይም በሌላ ምክንያት አለመረጋጋት ቢፈጠር። በዚህ ወቅት በክልሉ ሰው እና ንብረት ላይ ጥፋት ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት አለ።

አይ። ይህ ሊሆን አይችልም።
.አሁን ሁኔታዎች ተቀይረዋል።
.እዚህ ክልል ውስጥ ያለው "አዲሱ ትውልድ ነቅቶባቸዋል"።
.በሁለቱ ክልል መሪዎች መሀል አሁን ትብብር አለ።
.አሁን "በቄሮዎች" እና "በፋኖዎች" መሃል ትብብር አለ። ለምሳሌ፦ ባሕዳር ላይ የተደረገውን አቀባበል እና ናዝሬት ላይ የተደረገውን ምላሽ አቀባበል። የመሳሰሉ አስተያየቶች ሲሰጡ ይሰማሉ።

ነገር ግን። ምን ያህል የክልሉ ህዝብ ነው ዜና ማሰራጫውች የሚመለከተው እና ያለውን ትብብር አይቶ የተቀየረው? ሰላማዊ ባልሆነ የሥር አት ለውጥ ወቅት ወይም አለመረጋጋት ወቅት ስንቱ ነው እንኚህን ትብብሮች  አስታውሶ እና ትእግስት ኖሮት ከጥፋት የሚቆጠበው? በውጭ እና በሀገር ውስጥ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ክልል ሲገቡ እና ህዝቡን የየራሳቸውን አጀንዳ ሲያስተምሩት ስንት ሰው ነው የማይቀየረው?

**መፍትሄ መፈለግ ያለበትስ ማነው?**
መፍትሄ መፈለግ ያለባቸው በሃገር ውስጥ እና በሃገር ውጭ ባሉ ይመለከተናል በሚሉ፦ የፖለቲካ ድርጅቶች፥የሃይማኖት ተቋሞች እና ግለሰቦች። ሊሎችም ሀላፊነት የሚሰማቸው ናቸው።

አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር እንደ የኦህዴድ/ኢህአዴግ/ ሊቀመንበርነታቸው እና  በክልሉ ያሉትን ብሶቶች እና አመለካከቶች በቅርብ እንደሚያውቁ መሪ እነኚህን ጉዳዮች በተለይ ለማሻሻል በንግግራቸው ወቅት ያሉት ነገር የለም።

ስለ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ከተነሳ አይቀር፤ በተመሳሳይ ወቅት ከነበሩት የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ማስተያየት ይጠቅማል።

ንጉሡ እና አማካሪዎቻቸው ፃሃፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድን ከጠቅላያ ሚንስትርነት አንስተው በወቅቱ የለውጥ አራማጅ የሚባሉትን ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ሲተኩ። የንጉሡን ሹም ሽር የ ወቅቱ የእንቅስቃሴ መሪዎች "የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" ብለው በመተቸት "ፋታ" ነሱ።  ሆኖም ጠቅላይ ሚንስትሩ አዲስ ሕገ መንግስት እንዲረቀቅ በማድረግ እና "ሁዋይት ፔፐር" የሚል ፖሊሲ በማርቀቅ በተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ሞክረው ነበር።

ደርግ-ኢሠፓ የጠቅላይ ሚንስትር ሹር አድርጎ ቀድሞ "ሽብር ፈጣሪዎች እና ወንበዴዎች" ይላቸው የነበሩትን፤  ሥም ቀይሮላቸው "ተቃዋሚ ሀይሎች" ብሎ በጠቅላይ ሚንስትሩ የሚመራ ልኡካን ቡድን አውሮፓ  ውስጥ ድርድር በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ሞክሮ ነበር።

እንዳሁኖቹ "ፀረ ሠላም" እና "ፀረ ልማት ሀይሎች" መሆኑ ነው።

አዲሱ ጠቅላያ ሚንስትር ኢትዮጵያዊ ስሜት የሚፈጥር፥ ባጠቃላይ ብሔሮችን የሚያቀራርብ እና ለብዙ ሰው ተስፋ የሚሰጥ ንግግር አድርገዋል። የአዲሱን ጠቅላያ ሚንስትር ንግግር እና  የለውጥ አጋራቸው ናቸው የሚባሉትን የኦሮሚያ ክልል መስተዳደር ፕሬዝዳንት - "ቀድሞ የነበረው ጭቆና የመደብ ጭቆና ነበር እንጂ፤ የብሔር ጭቆና አልነበረም" ብለዋል የሚለውን- አነጋገር። ከቀድሞዎቹ የድርጅቱ እና የክልሉ መሪዎች አነጋገር ጋር ላነጻጸረ፤ የኦህዴድ/ኢህዲአግ/ " አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ተቀለበሰ እንዴ?ያሰኛል። ሆኖም የአዲሱ ጠቅላያ ሚንስትር ለሃገሪቱ ችግሮች ያላቸው ተጨባጭ መፍትሄ አሁንም እየተጠበቀ ነው።

**ለማጠቃለል።**

እንደተሰጋው ምንም ነገር ላይፈጠር ይችላል። መነጋገሩ እና መዘጋጀት ግን፤ ሰላማዊ ያልሆነ የስርአት ቢካሄድ ወይም በአለመርጋጋት ቢፈጠር በወቅቱ ጥፋት እንዳይደርስ ይጠቅማል የሚል የግል አስተያየት  አልኝ።

ጥፋት ከደረሰ በኋላም ማዘኑ እና ክንፈር መምጠጡ አይጠቅምም። የጠፋውን ሕይወት እና ንብረት አይመልስም።

በነበረው ማህበራዊ ግንኙነት እና በነበረው ሶሻሊስት ሥርአት ምክንያት ባለፉት ጊዜያት የደረሱት ጥፋቶች  ይደርሳሉ ብሎ አብዛኛው ሰው ቀደም ብሎ ያሰበ አይመስለኝም።

በተጨማሪ መነጋገሩ ኦህዴዲ/ኢ.ህአዴግ/ ባለፉት አመታት በተከተለው አሉታዊ እርምጃዎች የተፈጠሩትን ብሶቶች እና ጤናማ ያልሆኑ አመለካከቶች መፍትሄ ለመፈለግም ይጠቅማል።